# ዳግም ሳንነደፍ - ስልት እንንደፍ

የመከራ ስቃይ.. ቀንበር - ተሸክመን ለዘላለም፣
ተራርቀን፣ ተለያይተን፣ - ብቻችንን ስናዘግም፣
ጀርባችንን ተሰጣጥተን - ኢምንት እክል ሰበብ ፈጥረን፣
ላንወጣው፣ ላንዘልቀው፣ - ተነጣጥለን ለብቻችን...፣
እንዳልቻልነው በመገንዘብ- ልብ እንግዛ ያገር ልጆች፤
ላንድ ዓላማ! ላንድ ውጤት! - ላገር ማዳን እንመቻች!

ለናት አገር ሕይወት ብርሃን - ደማቅ ፋና ሳያበራ፣
የጀመርነው መንገድ ጉዞ፣ - እንዳይገታ በደንቃራ፣
ካሳለፍነው መራር ሕይወት - የጠጠረ ትምህርት ቀስመን፣
አውሎ ነፋስ ሳናስገባ - እጅ-ለእጅ ተያይዘን፣
ጊዜያችንን ሳናባክን - ባልባሌ ተረት ተረት፣
ይልቅ ታጥቀን እንነሳ - ኢትዮጵያን ለማስፈታት!

በጨለማ እስር ኑሮ - በሰቆቃ በግርፋት፣
ላገር ሕይወት ለሕዝብ ክብር - ለእምነታቸው በመሰዋት፣
ያገር ጥቃት ለመመከት - ባደባባይ በመፋለም፣
ለነጻነት ክቡር ዕሴት - የፈሰሰ ንጹሃን ደም፣
ሳይሞግተን ከመቃብር - የመስዋዕት ውጤት ዕዳ፣
ግብራችንን ለመወጣት - ለቃል እምነት እንሰናዳ!

የሦስት ሺህ ዘመን ክብር - ያለኝታነት ባለ አገር፣
የአበው ዕርካብ ታሪክ ውጤት - ለዝንተ-ዓለም እንዲሻገር፣
የቀመርነው ውጥን ራዕይ... - ባይደርስ እንኳ በኛ ዘመን፣
«...ሦርዶ አይብቀል» ዜማችንን - ከላያችን አስወግደን፣
ሩቅ በማለም እንታጠቅ - ለቅን ትግል እንነሳ፣
አዲስ ታሪክ ትተን እንሂድ - ለትውልዱ ሕያው ቤዛ!

ከእንቅልፋችን እንነሳ - ይከንክነን ምሳሌ-አበው...፣
«አወይ ፍርጃ! እባብ ሞኝን፣ ሁለት ጊዜ ነዳደፈው፤
አንዴ ሳያይ - ሳያስበው፣
ሌላ ጊዜ ደግሞ ሲያሳይ - እንዴት አርጎ እንደነደፈው፤»
ሁለቴውንም ተነድፈናል - ርግብ፣ የዋህ፣ ሞኞች እኛ፣
ባይምሬ ጠንቅ፣ በሚያደባ፣ በክፉ እባብ፣ በመርዘኛ!
ህልውና ሳያከትም - ለሦስተኛ ሳንነደፍ፣
ዘረ-ሐበሻ መላ ይምታ! ስልት እንንደፍ!!

ጌታቸው አበራ
ሐምሌ 1999 ዓ.ም.